የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሄራዊ ፓርቲ
ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY

# ፋኖ

*መጋቢት 01 2011 ዓ ም*

*ከኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ*

*ከኦሮሞ ሕዝብ ንቅናቄ ለኢትዮጵያ አንድነት የተሰጠ ማሳሰቢያ*

## *ሥልጣን ተርክቦ ከተጠያቂነት መሸሽ ከሃዲነት ነው!*

*ይብዛም ይነስም ኃላፊነት አደራ ነው፣ ኃላፊነትን በተቻለ መጠን መወጣት የኩሩ ሰው አንዱ ተግባር ነው፣ ኃላፊነትን በአግባቡ የማይወጣ በባህላዊም ሆነ በሕግ ተጠያቂ ነው፡፡*

*ለ27 ዓመት ሕዝባችንን ሲገድልና ሲያሣድድ የነበረውን ወያኔን ሲያስወግድ በወያኔ ምክር ቤት የተመረጠ ዶር አቢይ ሥልጣን እንደያዘ ትግራይ ሣይቀር በመላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲደገፍ ይሠራልናል፣ አንድነታችንን አጠናክሮ ከመበታተን ይታደገናል በማለት ነበር እንጂ የወያኔን የመለያየት ፈር አስፍቶ ይቀጥላል በሚል ጥርጣሬ አልነበረም፡፡*

*ዶር አቢይ ወደ ሥልጣን ከመጣ በኢትዮጵያ የደረሰውና በመድረስ ላይ ያለው ቀላል ግምት የሚሠጠው አይደለም፡፡ ከሁሉም በላይ ጎልቶ የሚታየው የብሔረሰቦች ፍጥጫ ዛሬ ከቁጥጥር ሥር እየወጣ ነው፡፡ ለዚህ ተጠያቂ የዶር አቢይ መንግሥት መሆኑ የምያጠያይቅ አይደለም፣ እንኳንስ የኢትዮጵያዊ ሰላምና ደህንነት ቀርቶ በኢትዮጵያ ምድር ላይ ለበቀለ ዛፍ አለአግባብ መጨፍጨፍ ወይም መቆረጥ ተጠያቂ የዶር አቢይ መንግሥት ነው፡፡*

*ዶር አቢይ በአዲስ አባባ ዙሪያ የተሠሩ ቤቶች በአቶ ታከለ ኡማ በጅ አዙር እንዲፈርሱ ሲደረጉ አላየሁም፣ አልሰማሁም፣ እኔ የከተማ አስተዳዳሪ አይደለሁም አይመለከተኝም ወዘተ የልጆች የእቃ እቃ ጫወታ እንጂ ከወጀለኛነት አያድንም፡፡*

*ዶር አቢይ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማስተዳደር ችሎታ ሣይሆን ፍላጎት እንደሌለው እኛ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሣንሆን ዓለም እየተረዳው ነው፡፡ የዶር አቢይ አመራር የከፋፍለህ አፋጃቸው የወያኔ ፖሊሲ እንጂ የኢትዮጵያውያን አጀንዳ አይደለም፡፡ ዛሬ በኢትዮጵያ መሬት ላይ ሰላም የሰፈነበት አከባቢ የለም፣ በአሁኑ ወቅት በአዲስ አባባና በዙሪያዋ የሚታየው ትንቅንቅ ጦሱ ወዴት እንደሚያመራ ለመተንተን ያዳግታል፡፡ ኢሕአዴግ በዶር አቢይ አመራር የበለጠ እንደሚጠናከርና የወያኔ ከፋፍይ ሕገ መንግሥት የበለጠ እንደሚጎለብት በራሱ አንደበት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ተናግሯል፡፡ ለዚህ ደግሞ ከጎኑ የቆሙት ለማ መገርሣ፣ ጀ WAR መሐመድ፣ ታከለ ኡማ ወዘተ ሕዝባችንን እያተራመሱ ናቸው፡፡የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ (ኢሕብፓ ) እና የኦሮሞ ሕዝብ ንቅናቄ ለኢትዮጵያ አንድነት (ኦሕን ኢአ) መጋቢት 01 2011 ዓ ም <<አዲስአባባ የኗሪዎቿ እንጂ የማንም አይደለችም >> በማለት በአክቲቭስት እስክንድር ነጋ የተጠራውንና የአዲስ አባባ ሕዝብ ያደረገውን ሰላማዊ ሰልፍ ሙሉ ለሙሉ መደገፋችንን ለአዲስ አባባ ሕዝባችን እንገልፃለን፡፡በተጨማሪም*

*በቅርብ ግዜ ውስጥ በኢትዮጵያ ክፍለ ሐገራት በሙሉ ተመሣሳይ ድርጊት እንዲደረግ እንማለዳለን። ከዚሁ ጋር በማያያዝ በየትኛውም ዓለም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ድጋፋቸውን ለአዲስ አባባ ሕዝብ እንዲለግሱ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን !!!*

## *ድል ለአንድነታችን !!*

## *አንድነታችን ኃይል ነው !!*

EPNP.INFO